# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

ቁጥር 141 ጥር 19 2003 ገጽ 1


አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

በቱኒዚያ የተቀጣጠለው ህዝባዊ አመጽ እንደ ሰደድ እሳት ወደ አካባቢው አገሮች እየተዛመተ ነው። ወላፈኑ አልጀሪያ፣ ሞሮኮና ሊባኖስን አዳርሶ አልባኒያ ደርሷል። አሁን የእሳቱ ሰደድ ግብጽና የመን ውስጥ በመንቦግቦግ ላይ ይገኛል።

ይህ የሰደድ እሳት አዲስ አበባ ሊደርስ ይችላል። ከላይ እንደተገለፀው ኢትዮጵያ ከሰሜን አፍሪካና መካከለኛ ምሥራቅ የምትጋራቸው በርካታ ባህርያት አሉ።

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## የቱኒዚያ ሕዝባዊ አመፅ ማእበል ሌሎች የአፍሪቃ ሃገራትን እያናወጠ መሆኑ ታወቀ

በቅርብ ጊዜ ቱኒዚያ ዉስጥ ሕዝባዊ አመፅ ከተቀሰቀሰና አመጹም ለቤን አሊ ተገቢዉን ዋጋ ከሰጠ በሁዋላ ተመሳሳይ አመጾች በግብጽ፣ አልጄሪያ፣ የመን ፣ እንዲሁም በዮርዳኖስ መቀጣጠላቸውን በርካታ የዜና አውታሮች በመግለጽ ላይ ይገኛሉ።

ከትናንት በስቲያ ጀምሮ በግብጽ የተለያዩ ከተማዎች ህዝባዊ አመጽ ተቀስቅሶ አራት ሲቪሎች መሞታቸውና በሙቶዎች የሚቆጠሩ ደግሞ መቁሰላቸው ታውቁአል፣ ፣

በተመሳሳይ መልኩ 18 የሚሆኑ የግብጽ ወታደሮች ላይ ጉዳት መድረሱ በተለያዩ የዜና አውታሮች ተዘግቦአል፣ ፣ ግብጻዊያን ያደረጉትን የተቃውሞ ሰልፍ ለመበተን የግብጽ ፖሊሶች አስለቃሽ ጪስና ውሃ መጠቀማቸውን የዜና አውታሮቹ አክለው ገልጸዋል።

ሆስኒ ሙባረክ በቅርቡ በአገራቸው ተደርጎ በነበረው ምርጫ እንደመለስ ዜናዊ 99፡6% የመራጭ ድምጽ አገኘሁ አይበሉ እንጂ በከፍተኛ የድምጽ ልዩነት ተቃዋሚዎቻቸውን እንዳሸነፉ ማስነገራቸው የሚታወስ ሲሆን አሁን ህዝባዊ አመጽ እያንቀጠቀጣቸው ባሉት የሰሜን አፍሪካ እና የመካከለኛ ምስራቅ አገሮች አንዳቸውም የመለስ ዜናዊ አይነት በዘር ላይ የተመሠረተ የአፓርታይድ አገዛዝ በአገራቸው እንዳልዘረጉ ይታወቃል።

በተመሳሳይ መልኩ አል-ጄሪያዎችም እንደ ቱኒዚያዎች በአደባባይ ሠልፍ ተቃዉሚቻዉን እንደቀጠሉ የዜና አውታሮች እየገለጹ ነው። በአልጀሪያ ሠልፍ-ተቃዉሞ ከተጀመረበት ጊዜ ጀምሮ በሰልፈኛዉና በፀጥታ አስከባሪዎች መካከል በተደረገ ግጭት አርባ-ሁለት ሰዎች መጎዳላቸው ይታወቃል። አል-ጄሪያን ለበርካታ አመታት የበጠበጠዉን የርስ በርስ ግጭት፥ ቁርቁስ ያስወገዱ፥ የኢትዮ-ኤርትራን ጨምሮ አፍሪቃ ሐገራትን ጠብ ፥ዉዝግብ ለማግረብ የጣሩ እየተባሉ ሲደነቁ፥ በምዕራቦች ሲወደሱ የነበሩት ፕሬዝዳት ቡተፊሊቃን ህዝባቸው በቁን በቃንዎት እያላቸዉ መሆኑም ታውቁአል።

በሌላም በኩል ይሄው በቱኒዚያ የተቀጣጠለዉ የህዝብ አመጽ በዮርዳኖስ ከሐገሪቱ ዘዉዳዊ አገዛዝ ይልቅ በጠቅላይ ሚንስትሩ በሚመራዉ መንግሥት ላይ ያነጣጠረ ተቃውሞ ተቀስቅሱአል። ንጉስ አብደላሕ የሕዝቡን ብሶትና ቁጣ «አዳምጬያለሁ» ለማለት፥ ጠቅላይ ሚንስትር መንግሥታቸዉ ተቃዉሞዉን ለማቀዝቀዝ የመሠረታዊ ሸቀጦች ዋጋን ለማስቀነስ ቃል ገብተዋል፣ ይሁን እንጂ በዮርዳኖስ የተቀሰቀሰው የህዝብ አመጽ ወዴት እንደሚያመራ የታወቀ ነገር የለም። (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ አወጣሁ ያለው የዋጋ ተመን የግብይት ቀውስ መፍጠሩ ተዘገበ

የወያኔው አምባገነን አገዛዝ የኑሮ ውድነትን ለመቆዋቆቆዋም በሚል ያወጣው የዋጋ ተመን ተግባራዊ ካለመሆን አልፎ አስፈላጊ የሚባሉ የምግብ ሸቀጦችን ሳይቀር ከገበያ ፈልጎ ማግኘት አስቸጋሪ እየሆነ መምጣቱን የ ቪ ኦ ኤው ዘጋቢ ፒተር ሃይላይን ገልጹአል፣ ፣ ፒተር በዘገባው የዋጋ ቁጥጥሩ በሃገሪቱ ግብይት ቀውስ መፍጠሩንና በሸማቹና የነጋዴው ማህበረሰብ ውጥረት ማስፈኑን በዚህም ምክንያት በርካታ ኢኮኖሚስቶችም የሁኔታውን አሳሳቢነት እያሳወቁ መሆናቸውን አክሎ ገልጹአል፣ ፣ እንደሃይላይን ዘገባ ባንዳንድ ቦታዎች ሸማቾች ከነጋዴዎች ጋር የተጣሉበትና የተጋጩበት ሁኔታም እንዳለ ታውቁአል።

በዘገባው ላይ አንድ ሸማች በሰጡት አስተያየት የወያኔው አምባገነን አገዛዝ ያወጣው የዋጋ ተመን ምንም የፈየደው ተግባር የለም፣ ፣ ቀደም ብለን መግዛት የምንፈልጋቸውን ሸቀጦች የመግዛት አቅም አልነበረንም፣ አሁን ደግሞ የሸቀጦች ዋጋ ቀንሱአል በመባሉ መግዛት የምንችል ሲመስለን ተፈላጊዎቹ ሸቀጦች ገበያ ላይ ሊገኙ አልቻሉም ብለዋል።

የወያኔው አገዛዝ ባለፈው መስከረም በወሰደው የብር የምንዛሪ አቅም ማስተካከያ እርምጃ የዶላርን ምንዛሪ በ17 አሳደግሁ ካለ ወዲህ ከውጭ በሚገቡ ዕቃዎች ላይ የዋጋው መጠን በእጅጉ ማናሩ ይታወቃል፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ ባለፈው ዓመት የኢትዮጵያ የንግድ አለመመጣጠን ከፍተኛ እንደነበረና ወደ 5.8 ቢልዮን ዶላር የንግድ ጉድለት እንደተመዘገበ መዘገቡ ይታውቃል፡፡

ዘረኛው የወያኔአገዛዝ ከተመን በላይ ሲሸጡ የተገኙ ከመቶ በላይ ቸርቻሪዎችን ሱቆች መዝጋቱንና እንዲህ ዓይነት የዋጋ ተመን ጥሰቶች ከተደጋገሙ ጣት መቁረጥ እንደሚጀምር የአገዛዙ ቁንጮ መለስ ዜናዊ ማስታወቁ ይታወሳል።

ከዚህ ጋር በተያያዘ የቀድሞው የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ኢኮኖሚስትና የግንቦት ሰባት ከፍተኛ አመራር አካል ዶር ታደሰ ብሩ የወያኔ የዋጋ ተመን ምንነት በሚል ለንባብ ባበቁት ጽሁፋቸው የኢትዮጵያ ህዝብ በከፋ ድህነት ውስጥ እየማቀቀ፤ ሰብዓዊ

ግዜ

ግንቦት 7 ዜና

ክብሩና ነፃነቱ በዘረኞች ተነጥቆ ኑሮውን በባርነት እየገፋ ባለበት ባሁኑ ሰዓት "የዋጋ ማሻሻያ አደረግን" ብሎ ማወጅ አንድም የተቃውሞ ኃይልን ለመከፋፈልና የህዝብን ትግል ለማዳከም የሚደረገውን ደባ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ነጋዴን በህዝብ ጋር ለማጋጫት ታቅዶ የተደረገ ስለመሆኑ ለሳፍታም መዘንጋት የለብንም ማለታቸው አይዘነጋም።

## አውስትራሊያ ለሀገሯ ዜጎች ወደ አዲስ አበባ እንዳይጓዙ ማስጠንቀቂያ ሰጠች

ከአውስትራሊያ በተሰማው ሰበር ዜና እንደተገለጸው በአዲስ አበባ የሚካሄደውን የአፍሪቃ ህብረት ስብሰባ ተከትሎ ሽብርተኞች በተለያዩ የአዲስ አበባ ከተማ ክፍሎች ፍንዳታዎች ሊያደርሱ እንደሚችሉ አውስትራሊያ ማስጠንቀቂዋ ታወቀ።

የአውስትራሊያ የውጪ ጉዳዮችና ንግድ ዲፓርትመንት ባወጣው በዚሁ መግለጫው አውስትራሊያዊያን ወደ ምስራቅ አፍሪቃ በተለይም ወደ አዲስ አበባ የሚያደርጉትን ጉዞ እንዲያቆሙ ወይንም እንዲያስቡበት አስጠንቅቁአል።

እንደ ዲፓርትመንቱ መግለጫ በአዲስ አበባ የሚካሄደውን የአፍሪቃ ህብረት ጉባኤ ተከትሎ ባልተገለጹ የአዲስ አበባ ክልሎች ሽብርተኞች ጥቃት ሊያደርሱ እንደሚችሉ ታማኝ የሆነ መረጃ እንደደረሰው አስታውቁአል፣ ፣ አያይዞም ወደ ኢትዮጵያ ለመጉአዝ ሃሳብ ያላቸው አውስትራሊያዊያን ከፍተኛ የሆነ ጥንቃቄ እንዲያደርጉ መክሩአል፡፡

ኢትዮጵያ ከዚህ በፊት ከኒውዮርክ ፍንዳታ አስቀድሞ የአልኢትሃድ የሽብር ጥቃት ዒላማ የነበረች ሲሆን፤በተለይም ከኒውዮርክ በፊት አዲስ አበባ፣ ድሬዳዋና ሐረር እንዲሁም በ አብዱል መጂድ ሁሴን እና በፕሬዚዳንት ሆስኒ ሙባረክ ላይ ከዛም በጎዮን፣ በዋቢ ሸበሌ፣ በትግራይ ሆቴል እና በምድር ባቡር ላይ የአልኢትሃድ አሸባሪዎች ጥቃት ዒላማ እንደነበረች ይታወቃል።

ኢትዮጵያ በተለይም በሶማሊያ ላይ ያደረገቺውን ወረራ ተከትሎ ከሽብርተኞች ጥቃት ሊደርስ እንደሚችል ሲዘገብ መቆየቱና በኢትዮጵያ የሚገኙ አብዛኛዎቹ ተቃዋሚ ፓርቲዎችም የወያኔው አምባገነን አገዛዝ በሶማሊያ ላይ የወሰደውን ርምጃ ሲቃወሙ መቆየታቸው አይዘነጋም።

## የወያኔው ዘረኛ አገዛዝ ዘር በማጥፋት ተግባር ላይ ያነጣጠረ ወንጀል መፈጸሙን ቀጥሉአል

በአማራ ክልል የደባርቅ ወረዳ ነዋሪዎች ለተላላፊ በሽታዎች ማገፊያ ተብሎ መድሃኒት በግዴታ እንደተሰጣቸውና ይህም መድሃኒት ላልታወቀ ሌላ በሽታ እየዳረጋቸው መሆኑን መናገራቸውን የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን ኢሳት ዘገበ።

ኢሳት በዘገባው የደባርቅ ነዋሪዎች እንደገለጹት የወረዳ የጤና ባለሙያዎች በየቀበሌዎቹ እየዞሩ የሰጡት መድሃኒት ነፍሰ ጡሮችን እያስወረደና ቀደም ብሎ የተለያዩ በሽታዎች ያሉባቸውን ሰዎች ላልታወቀ ሌላ በሽታ እንዲጋለጡ ያደረጋቸው መሆኑን ገልጹአል።

ለደባርቅ ነዋሪዎች መድሃኒቱ የተሰጠው ባካባቢው ያሉ ተላላፊ በሽታዎችን በማስወገድ ለጉብኝት የሚሄዱ ቱሪስቶችን ጤንነት ለመጠበቅ ነው መባሉን ኢሳት የዘገበ ሲሆን፣ ፣ የአካባቢዉ ነዋሪዎች እንደሚሉት ግን በዚህ ምንነቱ ያልታወቀ መድሃኒት የሞቱ ሰዎች ሳይኖሩ እንደማይቀሩ አክሎ ገልጹአል።

ዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ በዘር ላይ ያነጣጠር ጅምላ ግድያን ቀደም ብሎ ወደ ስልጣን ወምበር ከተቆናጠጠ ጀምሮ ሲፈጽም እንደቆየ የተለያዩ የመረጃ ምንጮች መዘገባቸው አይዘነጋም።

## በዘረኛውና አምባገነኑ አገዛዝ የሽብርተኞችን ደባ አከሸፍኩ በማለት ሲደነፋ መሰንበቱ ተዘገበ

በዘረኛውና አምባገነኑ መለስ የሚመራው የወንበዴ ቡድን በቁጥጥሩ ስር በሚገኘው የመገናኛ ብዙሀን ተሸርቦብኝ የነበረውን ጥቃት በተሳካ መልኩ አከሸፍኩ በማለት ሲደነፋ መሰንበቱን ዘጋቢያችን ከስፍራው በላከልን ሪፖርት አስታውቆናል።

እንደዘገባው ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ በቁጥር ሰባት የሚሆኑ የተባሉ ሽብርተኞች ከኤርትራ መንግስት የገንዘብና የስልጠና ድጋፍ ሲሰጣቸው የቆዩ መሆናቸውን ጠቅሶ በአፋር ክልል በኩል ወደ ኢትዮጵያ ሰርገው እንዲገቡና ሰላም እና አለመረጋጋት እንዲፈጠር እንዲያደርጉ የተላኩ ናቸው ሲል ከሱዋል። ዘረኛው አገዛዝ አያይዞም ሽብርተኛ ተብዬዎችን በቁጥጥር ስር ሲያውል በእጃቸው ላይ ከፍተኛ መጠን ያለው ገንዘብ፣ የነፍስ ወከፍ መሳሪያና ከባድና ቀላል ፈንጂዎችን እንደያዘ ጠቅሱዋል። ተቆጣጥሮት ባለው የቴሌቪዢን ጣቢያም አንደኛውን ሽብረተኛ ተብዬ ያቀረበ ሲሆን ሰውዬውም የወያኔው አገዛዝ እንዳለው ከኤርትራ መንግስት ለሽብር ስራ የተላከ መሆኑን መናገሩም ታውቁአል።

ይሁን እንጂ የዜናውን እውነተኛነት ለማጣራት ሽብርተኞች ናቸው የተባሉት በቁጥጥር ስር ዋሉባቸው በተባሉት የአፋር ጠረፋማ አካባቢዎች የተንቀሳቀሰው ዘጋቢያችን ወሬው ፈጽሞ ከእውነት የራቀና የፈጠራ መሆኑን የካባቢውን ነዋሪዎች ጠቅሶ ዘግቦአል። ለዘጋቢያችን ስማቸው እንዳይጠቀስ በመጠየቅ አስተያየታቸውን የሰጡት አንድ ያካባቢው አዛውንት ጉዳዩ ወያኔ ከገባ ጀምሮ በአፋር ህዝብ ዘንድ ተቀባይነት ያላገኘውና ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተጠናከረ በመጣው ተቃውሞ የተደናገጠው መለስ አካባቢውን ሙሉ በሙሉ በቁጥጥር ስር አውዬዋለሁ የሚል ስሜት በህዝቡ ዘንድ በመፍጠር ህዝቡን ለማስፈራራት የተጠቀመበት ዘዴ (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## ህዝባዊ አመጽ ከቱኒስ ወደ ካይሮ እና ሰንዓ፤ አዲስ አበባስ?

በቱኒዚያ የተቀጣጠለው ህዝባዊ አመጽ እንደ ሰደድ እሳት ወደ አካባቢው አገሮች እየተዛመተ ነው። ወላፈኑ አልጄሪያ፣ ሞሮኮና ሊባኖስን አዳርሶ አልባኒያ ደርሷል። አሁን የእሳቱ ሰደድ ግብጽና የመን ውስጥ በመንቦግቦግ ላይ ይገኛል።

ሰሜን አፍሪካና መካከለኛው ምሥራቅ በዓይነቱ ልዩ የሆነ የለውጥ ማዕበል ውስጥ ናቸው። የአምባነኖች ጡንቻ መፈርጠም፤ የተቃዋሚ ፓርቲዎች መዳከም ህዝቡን ከትግል እንዲሸሽ አላደረገውም። እንደ ቱኒዚያው መሃመድ ቦዛዚ እንደየመንዋ ታዋኮል ኮርማን ያሉ "እስካሁን በነበርንበት ሥርዓት ከምንቀጥል ህይወታችን ማጣት ይቀለናል" የሚሉ ወጣቶች ተበራክተዋል።

የአንባገነነት መንሰራፋት፤ "በመተካካት" ስም ስርወ-መንግሥት የማቋቋም ህልም፤ የፍትህ እጦት፤ የውሸት ምርጫዎች መብዛት፤ የሰብዓዊ መብቶች መረገጥ፤ የሥራ አጥነት መበራከት፤ የፓሊስ፣ ጦር ሠራዊትና እና "የጆሮ ጠቢዎች" መብዛት፤ የኑሮ መወደድ እና የተቃዋሚ ፓርቲዎች መዳከም ከቱኒዚያም ሆነ ከግብጽ ይልቅ የኢትዮጵያው አምባገነን መለያ ባህርያት ናቸው።

ለውጥ እንደ ወረርሽን የመሰራጨት ኃይል አለው። በአንዱ አገር የተነሳው ተቃውሞ ወደ ጎረቤት ለመዛመት ጊዜ አይፈጅበትም። እናም ቱኒዝያ የተጫረው እሳት በአንድ ወይም በሌላ መንገድ የሰሜን አፍሪካንና የመካከለኛ ምሥራቅ አገሮችን መንካቱ በጭራሽ የማይቀር ነገር ነው። በእነዚህ አገሮች ሁሉ የሥርዓት ለውጥ ከመጣ አዲስ ጂኦ-ፓለቲካ ይፈጠራል።

ይህ የሰደድ እሳት አዲስ አበባ ሊደርስ ይችላል። ከላይ እንደተገለፀው ኢትዮጵያ ከሰሜን አፍሪካና መካከለኛ ምሥራቅ የምትጋራቸው በርካታ ባህርያት አሉ። በኢትዮጵያውያን እየደረሰ ያለው ግፍና መከራ በግብጽም በየመንም ከበደረሰው በብዙ እጥፍ ይበልጣል፤ እኛ ዘንድ ያለው ችጋርም እነሱ ዘንድ ካለው ጊዜዓዊ ረሃብ ጋር የሚወዳደር አይደለም። አገራችን በአገር ውስጥ ቅኝ አገዛዝ ሥር በመሆኗ ህዝባዊ እምቢታን ካረገዘች ቆይቷል። ቅራኔዎች ለመፈንዳት ሰበብ መጠበቅ ከጀመሩ ውሎ አድሯል። ስለሆነም ዛሬ ካይሮና ሰነዓ እያየነው ያለው ህዝባዊ ትዕይንት ነገ አዲስ አበባ ውስጥ ልናየው እንችላለን።

ይህ መልካም ዜና ቢሆንም ሥጋትም አለብን። እኛ ኢትዮጵያውያን ወያኔ የተከለብን ተጨማሪ በሽታ ስላለብን ጥንቃቄዓችን የላቀ መሆን ይኖርበታል። ወያኔ በዘር ያደራጀው ጦር ከህዝብ ጋር ይወግናል ብሎ መጠበቅ እጅግ አስቸጋሪ ነው። ከዚህም በተጨማሪ ወያኔ የተከለብን ዘረኝነት እኛንም ጠልፎ እንዳይጥለን ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል።

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ የኢትዮጵያ ህዝብ ተባብሮ እንዲነሳ ይጠይቃል። እኛም ለመብቶቻችን መቆም ግዴታችን ነው ይላል። የነፃነትና የዲሞክራሲ ወገንተኛ የሆን ፓርቲዎች ሁሉ እየተፈጠረ ያለውን ሁኔታ በንቃት እንድንከታተል፤ ተመሳሳይ ሁኔታ በአገራችን ቢከሰት መከተል ስለሚኖርብን ስልቶች እንድንወያይና፤ በጋራም በግንባር ቀደምትነት እንድንቆም ያሳስባል። የወያኔ ዘረኛ አወቃቀር የትግላችንን አቅጣጫ እንዳያስት ሁላችንም በኃላፊነት እንንቀሳቀስ ይላል።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!**

● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ●

### ወያኔ በእርዳታ የሚያገኘውን ገንዘብ መመዝበሩን መቀጠሉ ተጋለጠ

ሀፍረት የሌላቸው የወያኔ ዘረኛ ገዢዎች ለሰብአዊ እርዳታ የሚገባውን ከፍተኛ መጠን ያለውን ገንዘብ ንጹሀንን ላማስፈራሪያ፡ ለማሰቃያና ለመግደያ ብሎም ኪሳቸውን ለማዳለቢያ እየተተቀሙበት መሆኑን ሰሞኑን ቤን ራውለንስ የተባሉ የሰብአዊ መብት ታጋይ ለአየር ላንድ ፓርላማ የውጭ ጉዳይ ኮሚቴ መግለጻቸውን ዘአይሪሽ ታይምስ የተባለው ጋዜጣ ዘግቡዋል።

ከዚህ ቀደም በሰር ቦብ ጊልዶፍ አስተባባሪነት በከፋ የረሃብ ችግር ለተጠቃው የሰሜኑ የሀገሪቱ ህዝብ ለመርዳት የተዋጣውን ገንዘብ ከተራበው ወገን አፍ በመቀማት የመሳሪያና የነሱ የተንደላቀቀ ኑሮ መምሪያ እንዳደረጉት ከበቂ በላይ በሆነ መረጃ ተደግፎ መቅረቡና በአለም ላይ መነጋገርያ ሆኖ መሰንበቱ የሚታወስ ነው። ይሁን እንጂ በውሸታቸው የሚታወቁት ግፈኞች በዛ አልበቃ ብሎአቸው አሁንም ከተላያዩ የተራድኦ ድርጅቶችና መንግስታት በሰብአዊ እርዳታ ስም የሚገኛውን በቢሊዮኖች የሚቆጠር ገንዘብ ችግረኞች እንዲደርሳቸው ከማረግ ይልቅ ራሳቸውና ጥቂት ደጋፊዎቻቸው እንደፈለጉ የሚንደላቀቁበት በተረፈው ደግሞ ለተቀረው ህዝብ የተለያዩ የፖለቲካ ደጋፊዎች ናችሁ በሚል የሚሳደዱበት የሚታሰሩበት የሚገደሉበት መሆኑን እኚሁ ግለሰብ ጠቅሰዋል።

አቶ ሮውለንስ አያይዘውም ሀገሪቱ በአለም ከፍተኛ እርዳታ ተቀባይ አገሮች ውስጥ አንዱዋ መሆኑዋንና በአመት ከሁለት ቢሊዮን ኢውሮ በላይ ገንዘብ እንደምታገኘ ገልጸው በተቃራኒው በሀገሪቱ ግን ከፍተኛ ረሃብ የመብት ረገጣና ግድያ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተስፋፋ መምጣቱ የሚያሳዝን መሆኑን ገልጸዋል። ጉዳዩንም ሁሉም የተራድኦ ድርጅቶችና መንግስታት ከበቂ በላይ መረጃ በተደገፈ መልኩ እንደሚኡያውቁት ተናግረዋል።

ጉዳዩን ሊያስተባብሉ ያልቻሉት የአየርላንዱ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ቃል አቀባይ ጉዳዩ ትኩረት ተሰጥቶት በአውሮፓ ህብረት በሚቁዋቁዋም አለም አቀፍ ቡድን ሊጠና ይገባዋል ሲሉ ተናግረዋል።

### የቱኒዚያ ሕዝባዊ አመፅ ማእበል ሌሎች . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ከዚሁ ዜና ጋር በተያያዘ የመንም በሕዝባዊ አመፅ እየታመሰች መሆኑአን የዜና አውታሮች በምስል አስደግፈው በመዘገብ ላይ ናቸው።

በተመሳሳይ ዜና እንደፈረንጆች አቆጣጠር ባለፈው ሳምንት ጃንዋሪ 14 ከሥልጣናቸው በህዝባዊ ተቃውሞ የተወገዱትና በአሁኑ ሰዓት በሳውዲ አረቢያ በስደት ላይ የሚገኙት የቱኒዚያው አምባገነን መሪ ቤኒ አሊና ባለቤታቸው በተገኙበት ተይዘው በቅጥጥር ሥር እንዲውሉ የቱኒዚያ ጊዜያዊ መንግሥት በትናንትናው ዕለት አለም አቀፍ የእስር ማዘዣ ማውጣቱ ታውቆአል። ቤን አሊ እና ቤተሰቦቻቸው በቁጥጥር ሥር እንዲውሉ የ እስር ማዘዣ የወጣባቸው በስልጣን ላይ በነበሩበት አመታት የአገራቸውን ገንዘብ በቢሊዮን የሚቆጠር ገንዘብና ንብረት በመዝረፋቸው ነው ተብሎአል።

በወያኔ ዘረኛ አገዛዝ ሥር ላለፉት 20 አመታት በመማቀቅ ላይ የሚገኘው የአገራችን ህዝብ እንደተቀሩት የሰሜን አፍሪካ አገሮች ሆ ብሎ ሊነሳና የመለስ ዜናዊንና ጥቂት ግብር አበሮቹን አገዛዝ ለፍጻሜ ሊያቃርበው ይችላል የሚለው ግምት የብዙ ኢትዮጵያዊያን እየሆነ መምጣቱን ሰሞኑን በተለያዩ የኢትዮጵያዊያን መወያያ መድረኮች ላይ የሚነሱት አስተያየቶች ያመለክታሉ።

### በዘረኛውና አምባገነኑ አገዛዝ የሽብርተኞችን ደባ . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

መሆኑን ተናግረዋል። አዛውንቱም በመቀጠል ወያኔ ከፍርሃቱ የተነሳ በክልል አዛውንት ሴቶችና ህጻናት ሳይቀሩ ሲያስር ሲገርፍና ሲገድል የቆየ መሆኑን ጠቅሰው ሽብርተኛ ከተባለም ከወያኔ በላይ ማን አለ ማለታቸውን ዘጋቢያችን ገልጽዋል፡፡

ወያኔ ከዚህ ቀደም በተደጋጋሚ በኦሮሚያ እና በ ሶማሌ አካባቢ ላይ በማተኮር የኦንግ እና የ ኦብነግ ደጋፊ ናችሁ በማለት በንጹሀን ዜጎች ላይ ግፍ ሲፈጽም መቆየቱ የሚታወቅ ሲሆን በተደጋጋሚም በሽብር ስራ ላይ ሊሰማሩ ሲሉ አገኛሁዋቸው በማለት የራሱን ሰዎች መሳሪያ በማሲያዝ በሚቆጣጠረው የቴሌቪዢን ጣቢያ ሲያቀርብ መቆየቱ የሚታወስ ነው።

### የወያኔው ገዢ ቡድን ሰሞኑን ነጋደዎችን እየከፋፈለ እና ለጥቃት እያዘጋጃቸውም መሆኑ ተዘገበ

ዘረኛው የወያኔ ገዢ ቡድን ከህዝቡ ገንዘብ ለመዘረፍ በማሰብ የለውጥ እቅድ በማለት ያወጣውን እቅድ ተግባራዊ ለማድረግ በሚል ስም አገኘዋለሁ ብሎ ያሰበውን ገንዘብ ማሰባሰብ የተሳነው መሆኑ የሚታወቅ ሲሆን ሰሞኑን የነጋዴው ህብረተሰብ ላይ ጫናውን በማብዛትና የተለያየ ተለጣፊ ስሞችን በመስጠት ለማስፈራራት እየሞከረ መሆኑን ከአዲስ አበባ ዘጋቢያችን አስታውቆናል።

የነጋዴው ማህበረሰብ በተደጋጋሚ የዘረኛው ቡድን ሰለባ ሆኖ መቆየቱ ቢታወቅም የእህል ዋጋ ንረትን ለመቆጣጠር በሚል ስም አብዛኛዎቹን ነጋዴዎችን ከጫዋታ ውጪ እንዳደረጋቸው መግለጻችን ይታወሳል።ይህ አልበቃ ብሎት ለነሱ የማይጠግብ ኪስ መሙያ የሚሆን ገንዘብ ለማሰባሰብ አዲስ እቅድ አወጣን በማለት እየተሩዋሩዋጡ መሆናቸው የሚታወቅ ሲሆን ለዚህም ተባባሪ በመሆን ገንዘብ የሚረዲዋቸውንና የነሱ ደጋፊዎች የሆኑትን ልማታዊ፡ ግዴታቸውን የሚወጡ ባለሀብቶች በማለት የሚያሞካሻቸው ሲሆን ከግብር ጀምሮ የተለያየ ጥቅማጥቅሞችን እንዲያገኙ እያደረጉ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ መብታቸውን ለመጠቀም የሞከሩትንና የዚህና የዚያ ብሄር አባላት ናቸው በሚል የከፈሉዋቸውን ነጋዴዎች ጥገኛ፡ ግዴታቸውን የማይወጡ ባለሃብቶች በማለት እያገለሉዋቸው መሆኑ ታውቁዋል። ለነዚህም ነጋዴዎች በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ ግብር እንዲጨምርባቸው አጋጣሚዎችን ሁሉ በመጠቀም በፍርድ ቤት የሚያንገላቱዋቸው መሆኑን ሪፖርተራችን አስታውቆናል።

ሪፖርተራችን በጉዳዩ ላይ ያናገራቸው አንድ ባለሀብት ከገንዘብም በላይ የገዢው ብድን አባላት በተለያየ ጊዜ በንግድና በመኖሪያ ቦታቸው በመሄድ የተለያየ ዛቻ እንደሚደርስባቸው ገልጽው ጉዳዩ ለህይወታቸውም እንደሚያሰጋቸው ተናገረዋል። በጉዳዩ ላይ አስተያየታቸውን የሰጡ አንድ የፖለቲካ ተንታኝ ደግሞ ችግሩ ዛሬ የተጀመረ እንዳልሆነ እና ወያኔ ስልጣኑን ከተቆጣጠረ ጀምሮ ሲተገብረው የቆየው ገበያውንና ሀገሪቱን በአንድ ቡድን ቁጥጥር ስር የማዋል እቅድ አካል መሆኑን ገልጸዋል። ዘረኛው ወያኔ የሚፈጽመውን አድልኦ ተቁዋቁመው እስካሁን የቆዩትን ባለሃብቶች ጭራሽኑም ስራቸውን ለአገዛዙ የንግድ ድርጅቶች አስረክበው እንዲወጡ የታቀደ መሆኑን ተናግረዋል።

ይሕ በእንዲህ እንዳለ ሰሞኑን ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ ያወጣው የዋጋ ተመን በሁሉም ነጋዴዎች ላይ እኩል ተግባራዊ እየሆነ እንዳልሆነ ሪፖርተራችን ነዋሪዎችን በመጠቆም አስታውቆናል። በተለያዩ የመዲናዋ ቦታዎች በመዘዋወር የከተማ ነዋሪዎችን ያናገረው ዘጋቢያችን ቁጥራቸው እጅግ ብዙ የሚሆኑ ነጋዴዎች ከተመን በላይ ሸጣችሁዋል በመባል የንግድ ቤታቸው እየታሸገ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ የገዢው ቡድን አባላትና ደጋፊዎች በመሆናቸው የሚታወቁ ባለሃብቶች እስካሁን ያለምንም ችግር ከዚህ ቀደም በነበረው ዋጋ እየሸጡ መሆናቸውን ገልጾልናል።

ነዋሪዎቾ እንደምሳሌ ያነሱዋቸውና ከተመን በላይ በመሸጥ ላይ አሉ ያሉዋቸውን ባለህብቶች ሳይቀር የዘረዘሩ ሲሆን በግንባር ቀደምትነት ግን በመዲናዋ 22 ተብሎ በሚታወቀው ስፍራ ሆሊውድ በመባል የሚታወቀው ባር ቢራ በ 15 ብር እየሸጡ መሆኑን ጠቅሰው ይህም እንደምሳሌነት ተነሳ እንጂ ድርጊቱ በሁሉም መጠጦች ላይም መሆኑን ጠቁመዋል።

ይህ አድሎአዊ አሰራር በርግጥ ዘረኛው ወያኔ የገዢው አባል ያልሆኑትን የንግዱን ማህበረሰብ ከስራ በማባረርና ራሳቸው በመቆጣጠር የሀገሪቱን ህብት ለመዝረፍ ያመቻቸው ዘንድ ያቀዱት የረዢም ጊዜ እቅድ መሆኑን ቁልጭ አድሪጎ የሚያሳይ ነው። ከዚህ ቀደምም በከተማይቱ የግብርን ተመን ለማሻሻል በማለትና በየ ባለህብቱ የንግድ ስፍራ በመዞር ምክንያታዊ ያልሆነና በግልጽ በዘርና በፖለቲካ አመለካከት ላይ የተመሰረተ ተመን ሲጣል መቆየቱ በዚህም ብዙ ባለህብቶች ለነፍሳቸው በመፍራት ሀገር ጥለው እንዲሰደዱ መደረጋቸው ይታወቃል።

በግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ የህዝብ ግንኙነትና
ቅስቀሳ ዘርፍ በሳምንት አንዴ የሚዘጋጅ ድርጅታዊ ልሳን

የፖስታሳጥን ቁጥር ፡- POBox: 4916
2003EX Haarlem, The Netherlands

# የወያኔ የዋጋ ተመን ምንነትና ለምንነት

(ዶ/ር ታደሰ ብሩ)

**“ሰባራ ዜና” እንደ “ሰበር ዜና”**

እንደምሰማው ከሆነ ዜናው ብዙ ሰዎችን አደናግሯል። አንዳንዶች “የተለመደ የወያኔ ማጭበርበሪያ ነው” በማለት ሲያጣጥሉት፤ ሌሎች ደግሞ “ዘገየ እንጂ መልካም ተግባር ነው” ሲሉ አወድሰውታል።

ለእኔ ዜናው ሰባራና አስቂኝ ነበር። አሁን ይህንን ማስታወሻ ስጽፍም እየሳቅኩ ነው። ያም ሆኖ ግን አንዳንዶች በዚህ ዜና መደሰታቸው ገርሞኛል፤ አስግቶኛልም። “ለካስ እኛ እንዲህ በትንሽና በማይመስል ነገር የምንታለል ነን?” እንድል አድርጎኛል። ይህንን ማስታወሻ እንድጽፍ ያነሳሳኝ አንዱ ምክንያትም ይኸው ስጋት ነው። እንዴት ይኸ ሰባራ ዜና ደህና ነገር ያመጣል ተብሎ ይታሰባል?

“ነገር በምሳሌ ...” እንዲሉ አስተያየቴን በምሳሌ ላስረዳ። አማካይ ክብደት ያለው ሠንጋ በሬ 5000 ብር እየተሸጠ ባለበት ሰዓት አንድ መወደድ የፈለገ ሹም “ከዛሬ ጀምሮ የአንድ በሬ ዋጋ 3000 ብር ነው” ብሎ አወጀ እንበል። መቸም በሬዎች ሁሉ እኩል አለመሆናቸው ለመረዳት አይቸግረንም። ሻጩም ገዢውም ይህንን ያውቃሉ። እናም አዋጁ እንደወጣ ሰዎች ምን እንደሚያደርጉ ለመገመት አያዳግትም። ሸማቹ አዋጁ እንደወጣ ተሯሩጦ ትልልቁን በሬ በ3000 ብር ይሸምታል። ይህ መብት ለሻጭ የተነፈገው ካልሆነ በስተቀር ሻጭም የራሱን በሬ በ3000 ብር መግዛት ያዋጣዋል (ይህ እንግዲህ “በሬ የመደበቅ ወንጀል” የማያሳስር ከሆነ ነው)። ጥቂት እድለኞች ተሯሩጠው ትላልቅ በሬዎችን በርካሽ መግዛት ይችሉ ይሆናል። ከትንሽ ጊዜ በኋላ ግን ገበያው አዲሱን ሥርዓት ይለምዳል። ትልልቆቹ ተሸጠው ያልቃሉ። ትንንሾቹ ደግሞ ከባለ 3000 ዎቹ በላይ እንዲደልቡ (እንዲወፍሩ) ገበያው አይፈቅድላቸውም። አዋጁ ባይኖር ኖሮ 1000 ብር ያወጣ የነበር ጥጃ ዛሬ 3000 ብር ስለተለጠፈበት ብቻ የሚገዛው ያገኛል ማለት አይደለም (ይህ እንዲሆን ሻጭን ብቻ ሳይሆን ገዢንም ማስገደድ ይጠይቃል)። አዲሱ ሥርዓት ሲለመድ ወደ ገበያ የሚመጡት በሬዎች ድሮም ቢሆን በ3000 ብር ሲሸጡ የነበሩት ዓይነት ብቻ ይሆናሉ። በሌላ አነጋገር በገበያ ውስጥ የምናያቸው በሬዎች እንደፋብሪካ እቃ ተመሳሳይ ይሆናሉ ማለት ነው። ማን ተጎዳ? ከረጅም ጊዜ አኳያ ከታየ ሻጭም ገዢም ሁሉም ተጎጂዎች ናቸው። የገበያ ኢኮኖሚ አንዱ ውበት አማራጮችን ማብዛቱ ነው። ዋጋ ስንወስን የጥራት አማራጮችን እናጠፋለን።

ለመሆኑ ምሳሌዬ ሊሆን የሚችል ነገር ነው? አስቸጋሪነቱ ግልጽ ቢሆንም በጭራሽ አይሆንም ብዬ አልከራከርም። የአላሙዲኑ ኤልፎራ፣ ዶሮዎች ላይ ይህንን ማድረግ ችሏል። በኤልፎራ ዶሮዎች መካከል እጅግም ልዩነት ስለሌለ ገዢዎች ሳይከራከሩ በውስን ዋጋ ይገዛሉ። በዶሮ የሆነው በበሬ ይሆናል?

አንዳንድ ሰዎች የዋጋ ቁጥጥር ያለና ወደፊትም የሚኖር በመሆኑ አዲስ ነገር እንዳልሆነ ይከራከራሉ። እውነታቸውን ነው። ነገር ግን ዝርዝር ውስጥ ገብተው የዋጋ ቁጥጥር መቸ፣ እንዴትና በምን ዓይነት ሸቀጦችና አገልግሎቶች ላይ ሊሆን እንደሚገባው መተንተን አይፈልጉም። በተለይም ደግሞ አሁን ተመን የተደረገባቸውን ሸቀጦች ባህርይ በመተንተን ስለ ተመኖቹ የረዥም ጊዜ ጠቀሜታና ተፈፃሚነት ማብራሪያ ሲሰጡ አላጋጠመኝም። ችግሩ ደግሞ ያለው ዝርዝር ውስጥ ሲገባ ነው። ለኤልፎራ ዶሮዎች የሆነው ለሀረርና ጅማ ሠንጋዎች ላይሆን ይችላል።

የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ የገበያ ኢኮኖሚ አይደለምና ለአስተዳደራዊ ዋጋዎች አዲሶች አይደለንም። በአገራችን የመብራት፣ የውሃ፣ የስልክ፣ የፓስታ አገልግሎች .... ዋጋዎች በገበያ ኃይሎች ተወስነው አያውቅም። ሸማች በእነዚህ አገልግሎቶች ዋጋ ላይ ይህ ነው የሚባል ተጽዕኖ የለውም። [በነገራችን ላይ የካ ክፍለ ከተማ ባለው የቴሌ ሂሳብ መቀበያ ቢሮ ውስጥ **“ደንበኛ ንጉሥ ነው!!!”** የሚል በትላላቅ ፊደላት የተፃፈ ጥቅስ አለ። ንጉሥነት ቀርቶ በቴሌ ዓይን ለሎሌነት እንኳን እንዳልበቃን ምርጫ 97 አሳይቶናል። በዚያ ወቅት መስማት የተሳናቸው ዜጎች SMS እንዳይዘጋ **ለምነው** ምላሽ አጥተዋል። መብራት ኃይል ሲያሻው “የዘወትር አገልጋያችሁ የሆነው የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክና መብራት ኃይል .....” እያለ መብራት እንደሚቋረጥ ይነግረናል። በ97 ከሚያዝያ 30 በኋላ ቅንጅት ስብሰባ በጠራባቸው ቦታዎች ሁሉ መብራት ይጠፋ እንደነበርም መረሳት የለበትም። በእንዲህ ዓይነት የተዛባ ሥርዓት ደንበኛ ንጉሥ ሳይሆን ባሪያ ነው።]

ወደ ሰባራው ዜና ልመለስ። እኔ የሥጋ ብልቶችን አላውቅም። ሆኖም ግን “በሥጋዎች” መካከል ያለው ልዩነት በበሬዎች መካከል ካለው ልዩነት የሰፋ እንደሚሆን እገምታለሁ። ሉካንዳ ቤቶች ብዙ የሥጋ ደረጃዎች እንደሚኖራቸው አልጠራጠርም። የክትፎ ሥጋ 90 ብር በነበረበት ጊዜም 52 ብር ይሸጡት የነበረ የሥጋ ዓይነት አይጠፋም። አዲሱ የዋጋ ተመን ከሠራ (ያውም ከሠራ ነው) የምንሸምተውን የሥጋ ጥራት ድሮ 52 ብር ይሸጥ ወደነበረው ደረጃ መውረዱ የማይቀር ነው።

ሌላው አማራጭ ደግሞ እንደ ቴሌ አይነት የመንግሥት ድርጅት አቋቁሞ ሥጋን የመቸርቸርን ኃላፊነት መስጠት ነው። ይህ ደግሞ የሸማቾችን ባርነት ጎትቶ ያመጣል። [በ97 እንደ ቴሌና መብራት ሁሉ የሥጋ እደላ በመንግሥት እጅ ቢሆን ኖሮ ምን ይፈጠር ነበር?]

ከላይ ስለ ሥጋ የተባለው ሁሉ ሩዝም ላይ ይሰራል። ከሃያ በላይ የሩዝ አይነቶች ኢትዮጵያ ገበያ ውስጥ እንዳሉ (ወይም እስከ አዋጁ እለት እንደነበሩ) ተነግሯል። አዲሱ ህግ በትክክል ሥራ ላይ ከዋለ የሩዝ ዓይነቶች ምርጫ “ተረት” ይሆናል።

**ስለ ሸቀጦችና አገልግሎቶች ጥራት**

ለሁሉም ነገር የጥራት ደረጃ አለው። የአንድ ሸቀጥ ወይም አገልግሎት እሴት የሚወስነው ደግሞ በጥራት ደረጃው ነው።

“ሩጫ ምን ማለት ነው?” ቢባል “ሩጫ ***በፍጥነት*** መራመድ ማለት ነው” ተብሎ ሊተረጎም ይችላል። “ፍጥነት” የጥራት መለኪያ ነው። በዚህ የጥራት መለኪያ የተለያዩ “መራመዶች” እጅግ የተለያዩ ደረጃዎች፤ በዚህም ሳቢያ እጅግ የተለያዩ እሴቶች /values/ አሏቸው። ዘገምተኛው መራመድ “በጎታታነት” ሲያሰድብ፤ ፈጣኑ መራመድ ደግሞ ዋንጫ ያስገኛል፤ ሚሊዮን ያሸልማል፤ ጀግና ያስብላል። ሁለቱ “መራመዶች” ገበያ ቢወጡ በገበያ ዋጋዎቻቸው መካከል የሰማይና የምድር ያህል ልዩነት ሊኖር ይችላል። በጨኸትና በዘፈን መካከል ያለውም ልዩነትም የጥራት ልዩነት ነው። ጨኸት ሊያሳምም ይችላል፤ ዘፈን ግን ይፈውሳል። እንዲህ ዓይነት በርካታ ምሳሌዎችን መዘርዘር ይቻላል። ጥራት ልፋትን ይጠይቃል። ጥራት ለሥራ ክብር መስጠትን፤ ለሸማች መጨነቅን፤ ቃል ማክበርን ይጠይቃል።

በአገራችን ያለውን የትምህርት (በተለይም የከፍተኛ ትምህርት)፣ የጤና አገልግሎት፣ የመንገዶችንና የከተማ ህንፃዎች አሰራር ላስተዋለ ወያኔ ያለበትን የጥራት ግንዛቤ ጉድለት የቱን ያህል አሳሳቢ እንደሆነ ይገነዘባል። የሰሞኑ የዋጋ ትመናም “ጥራት” የተሰኘው ጽንሰሃሳብ በወያኔ ፓሊሲ አውጪዎች (ፖሊሲ ካልነው ማለት ነው) ጭንቅላት ውስጥ አለመኖሩ ያሳየናል። ስለዚህም ነው በነሱ ጭንቅላት ውስጥ ሥጋ ሁሉ አንድ ዓይነት፤ ሩዝ ሁሉ አንድ ዓይነት፤ ደብተር ሁሉ አንድ ዓይነት፤ ሻይ ቅጠል ሁሉ አንድ ዓይነት ሆኖ የታያቸው።

**ስለ “ስግብግብ” ነጋዴዎች**

በሰሞኑ ዜና መነሻነት የኢትዮጵያ ነጋዴዎች የተለየ የስግብግነት ባህርይ አላቸው የሚሉ በርካታ አስተያየቶችን አንብቤዓለሁ። ለምን የኛ ነጋዴዎች እንዲህ ዓይነቱን ባህርይ እንዳዳበሩ ለማብራራት የሞከረ ግን አላጋጠመኝም።

የወያኔ ካድሬ በስነምግባር ጉድለት ነጋዴን ሲከስ መስማት የሚገርምም፤ የሚያሳዝንም ነው። ማን ማንን ነው በስነ ምግባር ጉድለት የሚከሰው? ነጋዴውስ ምን እንዲሆን ነው የሚጠበቅበት?

“በገበያ ኢኮኖሚ ነጋዴው የስነ-ምግባር ተገዥ እንዲሆን አይጠብቅበትም። የራሱን ጥቅም የሚያስጠብቅ ነጋዴ መኖር ለገበያ ኢኮኖሚ በቂ ነው” እያለ አጥብቆ የሚከራከር፤ እኔ የሱን ሃሳብ ስለምቃወም “ቢዝነስንና በጎ-አድራጎትን ታምታታለህ” የሚለኝ ጓደኛ ነበረኝ፤ መከራከሩን ተውነው እንጂ አሁን አለ። ለኢኮኖሚክስ ተማሪዎች የእሱን ክርክር መረዳት አዳጋች አይሆንም።

መሠረታዊው የኢኮኖሚክስ ቲዎሪ እንዳለ ሆኖ ቢዝነስ (ቢያንስ እኔ በምረዳው መንገድ) ከፍተኛ ስነምግባር የሚጠይቅ ማኅበራዊ ተግባር ነው ብዬ አምናለሁ። እኔ ከዚህም በላይ እሄዳለሁ። ንግድ (ቢዝነስ) ሰውን **ትሁት** ያደርጋል ብዬ አምናለሁ። ንግድ ደንበኛን (በዚያው ሰውን) ማክበርን ያስለምዳል። ትዕቢተኛ ሰው ነጋዴ መሆን አይችልም። እንዲህ በማመን የመጀመሪያው ሰው አይደለሁም፤ የመጨረሻም አልሆንም። ሁለት የቆዩ ጥቅሶችን እዚህ ጋር እንዳስገባ ይፈቀድልኝ።

> Commerce ...softens and polishes the manner of men.
> It is almost a general rule that wherever manners are gentle, there is commerce; and wherever there is commerce, manners are gentle.

ለእኔ ቴሌና መብራት ኃይል ነጋዴዎች አይደሉም ማለትም የቢዝነስ ኮርፓሬሽኖች አይደሉም። ለእኔ አላሙዲንና የወያኔ “ነጋዴዎች” ነጋዴዎች አይደሉም። ስለ ስግብግብ ነጋዴዎች ስናወራ እነማንን ማለታችን እንደሆነ ግልጽ መደረግ አለበት። የምንናገረው የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ ስለተቆጣጠሩት ሰዎችና ተቋማት ከሆነ ከስማቸው በስተቀር በሃሳቡ ስለምስማማ ይህንን ነጥብ እዚሁ እጨርሳለሁ። የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ የተቆጣጠሩት የወያኔና የአላማሙዲን ድርጅቶችና ሰዎች መሆናቸው የማያከራክር ጉዳይ ነው። እነሱ ዘራፊዎች እንጂ ነጋዴዎች አይደሉም። እነሱ የቢዝነስ ብቻ ሳይሆን ምንም ዓይነት ስነ- ምግባር የላቸውም። የምንናገረው ስለ ነጋዴዎች ከሆነ ግን የኢትዮጵያ ነጋዴዎች አሁን ተጋንኖ የሚነገረውን ያህል የጎላ የስነ-ምግባር ችግር አለባቸው ብዬ አላምንም።

እርግጥ ነው በመላው ማኅበረሰባችን ውስጥ እየደረሰ ያለው የስነምግባር መሸርሸር ነጋዴውን መንካቱ የማይቀር ነው። ውሸታም ጳጳስ፤ ውሸታምና ፈሪ “ሽማግሌ”፤ ለሞባይል ቀፎ የመንግሥትን በጀት የሚያጭበረብር የፀረ-ሙስና ኮሚሽነር ባለበት አገር “በገዛሁበት ነው የምሸጥልዎ” እያለ ጥቂት ሳንቲሞችን የሚያጭበረብር ባለሱቅ መኖሩ ለምን ይገርመናል?

ይህ የሚያመለክተው በስነምግባር ረገድ ብዙ መሥራት እንደሚኖርብን ብቻ ነው። በአንፃራዊ መልኩ ከታየ ግን በስነምግባር ረገድ የንግዱ ማኅበረሰብ ሰርቶ፣ ለፍቶ፣ ጥሮ በራሱ ጉልበትና ላብ ፍሬ የሚያድር፤ ለሌሎች የኅብረተሰብ ክፍሎች አርዓያ መሆን የሚችል ነው።

ይሁን እንጂ የወያኔ ሹማምንት ስለነጋዴዎች ስግብግብነት ሲያወሩ የገዛ ራሳቸውን ወይም በየቢሮው የሰገሰጓቸውን ሹሞቻቸውን ወይም በኮንትሮባንድ የተሰማሩትን የጦር መኮንኖቻቸውን እያሰቡ አይደለም። በስግብግብነት እየተወነጀሉ እየተዘጉ ያሉትም የችርቻሮ ሱቆች ናቸው። “ሩዝ ኪሎው በብር 12.50 ገዝተህ ኪሎው በብር 12.50 ሸጠህ አትርፍ” ተብለው ይህን ተግባራዊ ማድረግ የሚቻልበትን ጥበብ ገና ስላላገኙ ስግብግብ ተብለው ብዙ ሱቆች ተዘግተዋል።

**ፓሊሲ አውጪዎቹ እና ኢኮኖሚክስ**

የወያኔ የንግድ ሚኒስትር ዴኤታ ደንበኛ በሆኑበት ሆቴል የታዘቡትን “ህገወጥ” የዋጋ አጨማመር በምሳሌነት ተጠቅመው የሰጡት ገለፃ አስቂኝ ነው። (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## የወያኔ የዋጋ ተመን ምንነትና . . .

(ከገጽ 3 የዞረ)

እንደሚኒስትሩ ገለፃ የቅቤ ዋጋ መጨመር ቅቤ ባልገባባቸው ምግቦች ዋጋ ላይ ተጽዕኖ ማምጣት የለበትም። እንደሳቸው አገላለጽ በክትፎ ዋጋ ላይ የሚመጣ ለውጥ በሌሎች የምግብ ዓይነቶች ላይ ምንም ተፅዕኖ የለውም። ሌላ ምሳሌ ብወስድ "በኮካኮላ ላይ የሚመጣ የዋጋ ለውጥ ፒፕሲን ምን አገባው?" እያሉን ነው። ሰውየው ምን ዓይነት ኢኮኖሚክስ እንደተማሩ እግዜር ይወቀው። ገበያ ሸቀጦችን በተለያዩ መንገዶች የሚያያይዝ መሆኑ የአንደኛ ዓመት ኮርስ ነው።

ይህን አፍረን እንለፈው ብንል እንኳን ሌላም ግዙፍ ስህተት አለ። እንደሳቸው ገለፃ ከሆነ የሸቀጦችና አገልግሎቶች የገበያ ዋጋ የሚወሰነው ሸቀጦቹን ወይም አገልግሎቶቹን ለማምረት በወጣው ወጪ ነው። ይህ በግልብ ሲታይ እውነት ቢመስልም በጣም የተሳሳተ ኢኮኖሚክስ ነው። የገበያ ዋጋን በማምረቻ ወጪ ማስብ አቅርቦት /supply/ ላይ ብቻ ያተኮረ ግማሽ ኢኮኖሚክስ ነው። ኢኮኖሚክሱን ሙሉ ለማድረግ እሸማቹ ኪስ ውስጥ ያለው የገንዘብ ብዛት ማሰብ ይጠይቃል። በሌላ አገላለጽ ፍላጎትን /Demand/ እና የገንዘብ የመግዛት አቅምን እሂሳብ ውስጥ ማስገባት ግድ ነው። የሸቀጦችና አገልግሎቶች የገበያ ዋጋ የሚወስኑት ሸቀጦቹን ለማምረት በወጣው ወጪ ብቻ ሳይሆን በየሰው ኪስ ውስጥ ባለ የወረቀት ገንዘብ ብዛት ጭምርም ነው። ገበያ ውስጥ የወረቀት ገንዘብ እየበተኑ ነጋዴው ዋጋ ጨመረ ብሎ መውቀስ የሚያሳፍር ነው። ለብሄራዊ ባንክ የወረቀት ብተና ገበያ የሚሰጠው ምላሽ በዋጋ ላይ የሚጨመሩ ቁጥሮች መሆኑ እንዴት ሳያውቁ ቀሩ? ይህ የሶስተኛ ዓመት ኮርስ ነው።

### የፓሊሲው ቀዳዳዎች

ፓሊሲው ብዙ ቀዳዳዎች እንዳሉት ካሁኑ እየታየ ነው። አንዳንዱን ቶሎ ቶሎ አንስቼ ልለፍ።

1. ምርጥ ሥጋ መግዛት ከፈለጉ ለወንበር አሊያም ለአዋዜ ብለው ጠቀም ያለ ገንዘብ ይክፈሉ፤
2. ጥራት ያለው ሩዝ ከፈለጉ ሩዙን ለሚይዙበት ፌስታል ጠቀም ያለ ዋጋ ይክፈሉ፤
3. ራሳቸው ወያኔዎቹ ጥራት ያለው ሸቀጥ ይፈልጋሉና ሱፐር ማርኬቶች እንደ "ባለኮከብ" ሆቴሎች ተቆጥረው ከተመን ነፃ እንዲሆኑ የቀረበው "አቤቱታ" ተቀባይነት ማግኘቱ አይቀርም እናም አቅሙ ካልዎት የሚፈልጉትን እቃ ሱፐር ማርኬት ሂደው ይግዙ፤
4. ረሃብ ቀጠሮ የማይሰጥ ስለሆነ "ይታገሱ" ልልዎት አልችልም እንጂ ይኸ ፓሊሲ ከጥቂት ወራት በኋላ ጨርሶ መረሳቱ የማይቀር መሆኑን አይዘንጉ።

እዚህ ላይ አጽንዖት ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ ታሪፉ ተፈፃሚ እንዲሆን የሌሎች በርካታ ሸቀጦችና አገልግሎቶች ዋጋ መወሰን እንዳለበት ነው። አለበለዚያ "ቀዳዳው" ብዙ ነው። በተለይም ኪራይና ምንዳ (wage) ካልተስተካከሉ ታሪፉን ለማስፈፀም ምን ያህል እንደሚያዳግት ለማወቅ ከወር በላይ የሚፈጅ አይመስለኝም፤ የእነሱን ዋጋ መወሰን ደግሞ አረንቋ ውስጥ መግባት ነው። የገዛ ራሱን ኪስ ስለሚጎዳበት ወያኔ የኪራይ ዋጋን ለመወሰን የሚሞክር አይመስለኝም።

### "ፓሊሲው" ለምን? ለምን አሁን?

በመጨረሻ ላነሳ የምፈልገው ጉዳይ ወያኔ ይህንን ፓሊሲ ለምን ፈለገ? ለምንስ አሁን ፈለገው? የሚሉትን ጉዳዮችን ነው:: ለእነዚህ ጥያቄዎች ፈጣንና አጭር ምላሽ ለመስጠት አራት ነጥቦችን ማንሳት ይበቃል ብዬ አምናለሁ።

ግቡን ያልመታው የብር ምንዛሪ ምጣኔ ቅናሽ "እፍርት" ለመሸፈን፤

1. የብር ምንዛሬ በድንገት እንዲቀንስ በተደረገ ሰሞን "ቆራጡ" እርምጃ የአገሪቱን ኢኮኖሚ እንደሚያመነጥቅ ገለፃ ሲሰጥ ነበር። የሚገርመው ልክ እንዳሁኑ የቅቤና ሌጣ ምግቦች ምሳሌ ሁሉ ያኔም የምንዛሪው ለውጥ በገቢ እቃዎች ላይ ካልሆነ በስተቀር ሌሎችን ሸቀጦች አይነካም ተብሎ ነበር። ገበያው አልታዘዝ ስላለ ሰበብ መፈለግ አስፈላጊ ሆነ።
2. የትራንስፎርሜሽን መፈክር ባልተጠበቀ ፍጥነት መወየብ ያመጣው መደናገጥ፤
   ከዚህ በፊት "የመፈክር ኢኮኖሚ" በሚል አጭር ጽሁፍ እንደገለጽኩት የወያኔ ኢኮኖሚ የመፈክር ኢኮኖሚ ነው። የመፈክር ኢኮኖሚ መፈክሩ ሲሰቀል ይሟሟቅና መፈክሩ ሲወይብ እንዘጭ ይላል። የትናንስፎርሜሽን መፈክር ሳንጠግበው መወየብ ጀመረ። ስለሆነም ካሁኑ እቅዱ ያልተሳካባቸውን ምክንያቶች ማዘጋጀት ያስፈልጋል። አዲሱ ፓሊሲ "ስግብግብ ነጋዴ" የሚባል ምናልባትም "ነፍጠኛን" የሚተካ መደብ ፈጠረ።
3. የቱኒዚያ ክስተት የፈጠረው መረበሽ፤
   የቱኒዚያው ሃቅ መለስንና ማፍያ ቤተሰቡን ቢያሸብር ምንም ሊገርመን አይገባም። የንግድ ሚኒስትር ሚኒስትር ዴኤታ እንደገለጹት "የቱኒዚያው ችግር እዚህ እንዳይደገም" ብለው "የሱሪ በአንገት" ፓሊሲ ነደፉ።
4. አጀንዳ ማቀበል፤
   ወያኔ እንደተለመደው አንድ አጀንጃ አቀብሎን እኛ አጀንዳ ላይ ስንራኮት እሱ አገር የመበትን ሥራዉን ያቀላጥፋል።
5. እርስ በርስ ማጋጨት፤
   ከሁሉም በላይ ዋነኛው ምክንያት የምለው ይህ ነው። ወያኔ በተገኘው መንገድ ሁሉ ከፋፍሎን እርስ በርስ ሲያጣላን ኖሯል። በዘርና በሃይማኖት የማጣላቱን ሴራ የተመኘውን ያህል ባይሆንም ጥሩ ውጤት አምጥቶለታል። አሁን ደግሞ የሥራ ዘርፍ አንዱ የመከፋፈያ መንገድ ሆኖ ቀርቧል። ወደፊት ደግሞ ምናልባት ወጣትና ጎልማሳ፤ ወንድና ሴት ለያይቶ ያጣላን ይሆናል።

### ማሳረጊያ

ወያኔ እስካሁን ከተዋጣለት ነገሮች አንዱ በየጊዜው ኢትዮጵያዊያንን እርስ በእስ ማናከስ መቻሉ ነው። አማራና ኦሮሞ፤ አፋርና ሶማሌ-ኢሳ፤ ስልጤና ጉራጌ፤ አኝዋክና ኑዌር .... እስላምና ኦርቶዶክስ፤ ኦርቶዶክስና ፕሮቶቴስታንት፤ ፕሮቴስታንትና ፕሮቴስታንት፤ ኦርቶዶክስና ኦርቶዶክስ፤ እስላምና እስላም ... ወያኔ በተገኘው ስንጥቅ ሁሉ እየገባ እርስ በርስ አናክሶን ተንሰራፍቶ ለመግዛት ችሏል። አሁን ደግሞ የመንግሥት ሠራተኛንና ነጋዴን ለማጣላት ቆርጦ ተነስቷል።

አንዳንድ ሰዎች ወያኔ በፈጠረው የኑሮ ችግር እጅግ በመጎዳታቸው መፍትሄ የተባለ ነገር ሁሉ ቢሞከር "ይሠራ ይሆናል" የሚል ባዶ ተስፋ የሚሳድሩ ሆነዋል። ወያኔ ደግሞ የህዝባችንን ተስፈኛነትና የዋህነት ለራሱ ጥቅም ያውለዋል። ትግላችን ውጤት እንዲያፈራ ወያኔ በሚሄበት መንገድ ሁሉ እየተከታተልን፤ የተንኮል ሴራዎቹን ማጋለጥ መቻል አለብን። ሰባራ ዜናዎችን "ሰበር ዜና" ማለትን መተው መቻል አለብን።

ከዚህም በተጨማሪ በየጊዜው በሚወረወሩልን አጀንዳዎች ሳቢያ ትኩረታችን እንዳይዛባ መጠንቀቅም ይኖርብናል። የኢትዮጵያ ህዝብ በከፋ ድህነት ውስጥ እየማቀቀ፤ ሰብዓዊ ክብሩና ነፃነቱ በዘረኞች ተነጥቆ ኑሮውን በባርነት እየገፋ ባለበት ባሁኑ ሰዓት "የዋጋ ማሻሻያ ኣደረግን" ብሎ ማወጅ አንድም የተቃውሞ ኃይልን ለመከፋፈልና የህዝብን ትግል ለማዳከም የሚደረገውን ደባ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ነጋዴን በህዝብ ጋር ለማጣላት ታቅዶ የተደረገ ስለመሆኑ ለኣፍታም መዘንጋት የለብንም።

***

## የወያኔው ገዢ ቡድን ሰሞኑን ነጋደዎችን እየከፋፈለ እና ለጥቃት እያዘጋጃቸውም መሆኑ ተዘገበ

ዘረኛው የወያኔ ገዢ ቡድን ከህዝቡ ገንዘብ ለመዘረፍ በማሰብ የለውጥ እቅድ በማለት ያወጣውን እቅድ ተግባራዊ ለማድረግ በሚል ስም አገኘዋለሁ ብሎ ያሰበውን ገንዘብ ማሰባሰብ የተሳነው መሆኑ የሚታወቅ ሲሆን ሰሞኑን የነጋዴው ህብረተሰብ ላይ ጫናውን በማብዛትና የተለያየ ተለጣፊ ስሞችን በመስጠት ለማስፈራራት እየሞከረ መሆኑን ከአዲስ አበባ ዘጋቢያችን አስታውቆናል።

የነጋዴው ማህበረሰብ በተደጋጋሚ የዘረኛው ቡድን ሰለባ ሆኖ መቆየቱ ቢታወቅም የእህል ዋጋ ንረትን ለመቆጣጠር በሚል ስም አብዛኛዎቹን ነጋዴዎችን ከጫዋታ ውጪ እንዳደረጋቸው መግለጻችን ይታወሳል።ይህ አልበቃ ብሎት ለነሱ የማይጠግብ ኪስ መሙያ የሚሆን ገንዘብ ለማሰባሰብ አዲስ እቅድ አወጣን በማለት እየተሩዋሩዋጡ መሆናቸው የሚታወቅ ሲሆን ለዚህም ተባባሪ በመሆን ገንዘብ የሚረዷቸውንና የነሱ ደጋፊዎች የሆኑትን ልማታዊ፡ ግዴታቸውን የሚወጡ ባለሀብቶች በማለት የሚያሞካሻቸው ሲሆን ከግብር ጀምሮ የተለያየ ጥቅማጥቅሞችን እንዲያገኙ እያደረጉ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ መብታቸውን ለመጠቀም የሞከሩትንና የዚህና የዚያ ብሄር አባላት ናቸው በሚል የከፈሉዋቸውን ነጋዴዎች ጥገኛ፡ ግዴታቸውን የማይወጡ ባለሃብቶች በማለት እያገለሉዋቸው መሆኑ ታውቁዋል። ለነዚህም ነጋዴዎች በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ ግብር እንዲጨምርባቸው አጋጣሚዎችን ሁሉ በመጠቀም በፍርድ ቤት የሚያንገላቱዋቸው መሆኑን ሪፖርተራችን አስታውቆናል።

ሪፖርተራችን በጉዳዩ ላይ ያናገራቸው አንድ ባለሀብት ከገንዘብም በላይ የገዢው ብድን አባላት በተለያየ ጊዜ በንግድና በመኖሪያ ቦታቸው በመሄድ የተለያየ ዛቻ እንደሚደርስባቸው ገልጽው ጉዳዩ ለህይወታቸውም እንደሚያሰጋቸው ተናገረዋል። በጉዳዩ ላይ አስተያየታቸውን የሰጡ አንድ የፖለቲካ ተንታኝ ደግሞ ችግሩ ዛሬ የተጀመረ እንዳልሆነ እና ወያኔ ስልጣኑን ከተቆጣጠረ ጀምሮ ሲተገበረው የቆየው ገበያውንና ሀገሪቱን በአንድ ቡድን ቁጥጥር ስር የማዋል እቅድ አካል መሆኑን ገልጸዋል። ዘረኛው ወያኔ የሚፈጽመውን አድልኦ ተቁዋቁመው እስካሁን የቆዩትን ባለሃብቶች ጭራሽኑም ስራቸውን ለአገዛዙ የንግድ ድርጅቶች አስረክበው እንዲወጡ የታቀደ መሆኑን ተናግረዋል።

ይሕ በእንዲህ እንዳለ ሰሞኑን ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ ያወጣው የዋጋ ተመን በሁሉም ነጋዴዎች ላይ እኩል ተግባራዊ እየሆነ እንዳልሆነ ሪፖርተራችን ነዋሪዎችን በመጠቆም አስታውቆናል። በተለያዩ የመዲናዋ ቦታዎች በመዘዋወር የከተማ ነዋሪዎችን ያናገረው ዘጋቢያችን ቁጥራቸው እጅግ ብዙ የሚሆኑ ነጋዴዎች ከተመን በላይ ሽጣችሁዋል በመባል የንግድ ቤታቸው እየታሸገ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ የገዢው ቡድን አባላትና ደጋፊዎች በመሆናቸው የሚታወቁ ባለሃብቶች እስካሁን ያለምንም ችግር ከዚህ ቀደም በነበረው ዋጋ እየሸጡ መሆናቸውን ገልጾልናል።

ነዋሪዎች እንደምሳሌ ያነሱዋቸውና ከተመን በላይ በመሸጥ ላይ አሉ ያሉዋቸውን ባለህብቶች ሳይቀር የዘረዘሩ ሲሆን በግንባር ቀደምትነት ግን በመዲናዋ 22 ተብሎ በሚታወቀው ስፍራ ሆሊውድ በመባል የሚታወቀው ባር ቢራ በ 15 ብር እየሸጡ መሆኑን ጠቅሰው ይህም እንደምሳሌነት ተነሳ እንጂ ድርጊቱ በሁሉም መጠጦች ላይም መሆኑን ጠቁመዋል።

ይህ አድሎአዊ አሰራር በርግጥ ዘረኛው ወያኔ የገዢው አባል ያልሆኑትን የንግዱን ማህበረሰብ ከስራ በማባረርና ራሳቸው በመቆጣጠር የሀገሪቱን ህብት ለመዝረፍ ያመቻቸው ዘንድ ያቀዱት የረዢም ጊዜ እቅድ መሆኑን ቁልጭ አድሪጎ የሚያሳይ ነው። ከዚህ ቀደምም በከተማይቱ የግብርን ተመን ለማሻሻል በማለትና በየ ባለህብቱ የንግድ ስፍራ በመዞር ምክንያታዊ ያልሆነና በግልጽ በዘርና በፖለቲካ አመለካከት ላይ የተመሰረተ ተመን ሲጣል መቆየቱ በዚህም ብዙ ባለህብቶች ለነፍሳቸው በመፍራት ሀገር ጥለው እንዲሰደዱ መደረጋቸው ይታወቃል።


**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ**
**የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

**በ 7140፣ 7175፣ 7185 KHZ በ 41 ሜትር ባንድ እና በ 6100 KHZ በ 49 ሜትር ባንድ**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ፣ ሐሙስ እና ቅዳሜ ከጠዋቱ 3፡00 ሰዓት እስከ 3፡30፤ እንዲሁም ከምሽቱ 2 ሰዓት እስከ 2፡30 የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።



**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org